## ወላጆች ስለልጆቻቸው የትምህርት ወይም የስነምግባር ሁኔታ የሚያሳስባቸው ከሆነ ምን ምን ነገሮችን ሊያደርጉ ይችላሉ?

- ❑ የልጅዎን የትምህርት ወይም የስነ ምግባር ሁኔታ ጉዳይ ለልጅዎ አስተማሪ ወይም አማካሪ ያሳውቁና በትምህርት ቤቱ "መደበኛ እገዛ" እንዳለ ይጠይቁ። ካልሆነ፣ የትምህርት ቤቱን ችግር ፈቺ ቡድን ያነጋግሩ።

- ❑ የልጅዎን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በተማለከተ መረጃ ያሰባስቡ። የልጅዎን ሁኔታ በተመለከተ ማቅረብ የሚትችሉት ማንኛውም መረጃ፣ ለምሳሌ የችሎታው/ዋ ደረጃ፣ ስለትምህርት ቤት ያለው/ያላት አስተሳሰብ፣ የፈተና ውጤቶች፣ የቀድሞ ትምህርት ቤቱ/ቷ ሁኔታ፣ ወይም ከጓደኞቹ/ቿ ጋር ያለው/ያላት ቀረበታና የመሳሰሉት መረጃዎች ሊጠቅሙ ይችላሉ።

- ❑ የልጅዎን ጠንካራ ጎኖችና ፍላጎቶች በተመለከተ ከሚመለከታቸው የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ጋር ያለውን ሁኔታ ለማሻሻልና ችግሮችን ለመፍታት በጊዜው ይወያዩ።

- ❑ የልጅዎን የትምህርትና የጠቅላላ እድገት ሁኔታ ለመከታተልና ለልጅዎ የመረጡት እገዛ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ከትምህርት ቤትዎ ጋር አብረው ይስሩ።

- ❑ **ማስታወሻ፤** ለልጁ/ጇ አስፈላጊው *"Response to Intervention (RtI)"* የሚባል የጣልቃ ገብ እገዛ እየተደረገለት/እየተደረገላት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም የልጁ/ጇ ጠቅላላ መረጃ ቀጣይ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው/እንደሚያስፈልጋት የሚያመላክት ከሆነና **"Special education"** የሚባል የልዩ ትምህርት ድጋፍ ለማግኘት መስፈርቱን የሚያሟላ/የሚታሟላ ከሆነ የልዩ ትምህርት ድጋፍ መስጠት ሁኔታ ውሳኔ ላይ ይደረሳል። በዚያን ጊዜ ለልዩ ትምህርት ድጋፉ መስጠት ውሳኔ የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልጋል።

***"Problem-Solving Teams" የሚባሉ ችግር ፈቺ ቡድኖች በልጅዎ ትምህርት ቤት ሌላ ስም ሊኖራቸው ይችላሉ፣ ለምሳሌ " FLEX" ወይም "CARE" ቡድን ሊሆን ይችላል።**

***የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት የሁሉንም ተማሪዎች የትምህርት ውጤት ለማሻሻል "RtII" የሚባል የጣልቃ ገብ ድጋፍና ውጤት ሂደትን ይከተላል።***




የኮሎራዶ ፖሊሲ መግለጫ

*"Response to Intervention (RtI)" የሚባል የጣልቃ ገብ እገዛ ውጤት፤ የአፈጻጸም መመሪያ* (የኮሎራዶ ትምህርት ቢሮ፣ 2008) የትምህርት ቤት ችግር ፈቺ ቡድን፣ የተማሪን ፍላጎት ባገናዘበ ሁኔታ፣ የተገኘውን የተማሪ የትምህርትና ጠቅላላ የተማሪ ክንውን መረጃ ዓይነትና የተደረገውን የጣልቃ ገብ እገዛ ሁኔታ እንደሚወስን የመላክታል። የጣልቃ ገብ እገዛ ዓይነትና መጠን በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ ይሞረኮዛሉ፣ የተማሪው/ዋን ዕድሜ/የክፍል ደረጃ ጨምሮ፣ ለልጁ/ጇ እየተደረገ ያለው የችሎታ እገዛ፣ እንደዚሁም የትምህርት ክንውን ክፍተት አስፈላጊነት ሊሆኑ ይችላሉ። የተገኘው የተማሪው/ዋ የትምህርት ክንውን መረጃዎች ዓይነትና ብዛትም ይለያያሉ። የጣልቃ ገብ ድጋፉ መጠን እየጨመረ ሲሄድ፣ የድጋፉ ውጤት ክትትል ብዛትም አብሮ መጨመር አለበት። የግል ግምገማ የተማሪው/ዋን የትምህርትና የጣልቃ ገብ ድጋፎች የማሟላት ጥረት ውስጥ አስፈላጊ ተግባር ነው።

*ተማሪ "RtI/Problem-Solving" የሚባሉ በጣልቃ ገብ ውጤት/ችግር ፈቺ ቡድን አማካይነት የድጋፍ አገልግሎት የሚሰጠው/የሚሰጣት ከሆነ፣* ትምህርት ቤቱ ጉዳዩን አስመልክቶ ለወላጆች የሚከተሉትን የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት፤

- ለተማሪው/ዋ የሚደረግ ጣልቃ ገብ ድጋፍ (የተማሪው/ዋን የትምህርት አቀባበል ለማሻሻል የሚጠቀሙት የማስተማር ዘዴዎች)፣ በተጨማሪም
- ከተማሪው/ዋ የሚጠብቁት የትምህርትና ሌላ የመረጃ ዓይነቶች ናቸው።

ከኮሎራዶ የትምህርት ቢሮ የተወሰደ፣ 2008

**"RtI"** በሚባል የተማሪ ጣልቃ ገብ የትምህርት ድጋፍ ዋና ቢሮ የተዘጋጀ መጽሔት

ለ Dr. Eleanor Harrison የላቀ ምስጋናን እናቀርባለን

ኢሜል፤
**rticentral@cherrycreekschools.org**
የስልክ ቁጥር፤ 720-554-4544

Dedicated to Excellence
Cherry Creek Schools

# የጣልቃ ገብ የትምህርት ድጋፍና ውጤት ማጠቃለያ "RtII" የሚባል የችግር መፍታት ሂደት

ለቼሪ ክሪክ ቤተሰቦችና ማህበረሰብ በሙሉ

**የትምህርት ቤትዎ ተወካይ**

______________________________
ስም

______________________________
የስልክ ቁጥር

______________________________
ኢሜል

ለልጄ የሚደረጉ ጣልቃ ገብ የትምህርት/የስነ ምግባር ድጋፎች

1) ______________________________

2)______________________________

3)______________________________

**2010 የተሻሻለ**

# የልጆቻቸው ጉዳይ ለችግር ፈቺ ቡድን እንዲወያዩበት ሲተላለፍ ወላጆች ከቡድኑ ምን ምን ነገሮችን ሊጠብቁ ይችላሉ?

**ከውይይቱ በፊት-**

- ያለዎትን ጉዳይ ለመወያየትና ለስብሰባ ለመቀጣጠር የልጅዎ አስተማሪ ይደውልልዎታል/ትደውልልዎታለች።
- ለእቅዳችን እንዲረዳን መረጃ ሞልተው እንዲመልሱልን መጠይቅ እንልክላችኋለን።

በውይይቱ ጊዜ-

- በስብሰባው ላይ ከ 4-10 የሚደርሱ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ባልደረቦች ሊሳተፉ ይችላሉ።
- ስብሰባው በልጅዎ የትምህርት ውጤት ማሻሻል ላይ ያተኮራል (ልጅዎ የሚያውቃቸውንና መስራት የሚችላቸው ነገሮች ያጠቃልላል)።

**ሊገኙ የሚችሉ ውጤቶች-**

- ሁሉም ተማሪዎች ለቀጣይ ስብሰባዎች ቀጠሮ ይሰጣቸዋል (ብዙ ጊዜ ከ6-10 ሳምንታት ውስጥ)
- የተወሰኑ ተማሪዎች ግባቸውን ደርሰው ከመጀመሪያ ጣልቃ ገብ የትምህርት/የስነ ምግባር ድጋፍ ካገኙ በኃላ ከሂደቱ ይወጣሉ።
- የተወሰኑ ተማሪዎች ጣልቃ ገብ ድጋፉን በቀጣይነት ሲያገኙ፣ ለሌሎች ደግሞ  አዲስ ዓይነት ጣልቃ ገብ ድጋፍ ይሞከራል።
- የተወሰኑ ተማሪዎች የ “ልዩ ትምህርት” ድጋፍ እንዲያገኙ ሊወሰን ይችላል።*
- ለሌሎች ለተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ  “ክፍል 504” የሚባል አገልግሎት ሊሰጣቸው ይችላል።

* ለ “ልዩ ትምህርት” መስፈርት ውሳኔ መስጠት የወላጅ ፈቃድ ያስፈልጋል።




የትምህርትና የጣልቃ ገብ ድጋፍ/የችግር ፈች ሂደት ውጤት ከቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች የመማር-ማስተማር ሂደት ጋር ይስማማል

- ❑ **አቅድ (Plan)፤** ቡድኑ ከትምህርት ቤትና ከቤት ያሰባሰበውን መረጃ በመተንተን የተማሪው/ዋን ጠንካራ ጎንና ምን ምን ድጋፎች እንደሚያስፈልጋት/እንደሚያስፈልገው ይለያል-- ውስን የትኩረት ጉዳዮችን መለየት፣ ግልጽና ሊለካ የሚችል የግብ ረቂቅ/እቅድ ማውጣት፣ እንደዚሁም ግቡን ለማሳካትና የግቡን ሂደትና መሻሻል ለመቆጣጠር የተለያዩ አማራጮችን ማሰላሰል።
- ❑ **አስተምር (Teach)፤** ቡድኑ እቅድን በማውጣት ሥራ ላይ ያውላል፣ የተማር የትምህርት/የስነ ምግባር መሻሻልን ዘወተር በተከታታይነት ይቆጣጠራል፣ በተጨማሪም ለክለሳና ለቀጣይ እርምጃ መራጃን ይሰበስባል።
- ❑ **ተቆጣጠር (Monitor)፤** የተደረገው የትምህርት/የስነ ምግባር ጣልቃ ገብ ድጋፍ በተመለከተ የተማሪው/ዋን  ምላሽ (ውጤት) እና የተደረገውን ጣልቃ ገብ ድጋፍ ውጤታማነት ለመገምገም ቡድኑ እንደገና ይገናኛል።
- ❑ **አስተካክል (Adjust)፤** ተማሪው/ዋ የተቀመጠውን ግብ ጋር መድረሱን/መድረሷን ወይም ከዚያም በላይ ማከናወኑ/ኗን ለመገምገም፣ እንደዚሁም የተማሪው/ዋ በፕሮግራሙ የመቀጠል ወይም ያለመቀጠል፣ የፕሮግራም ለውጥ የማድረግ፣ ወይም ፕሮግራሙን የመጨረስ ሁኔታ ጨምሮ የ “ቀጣይ እርምጃ” ውሳኔን ለመውሰድ ዓላማ ቡድኑ የተሰበሰበውን የተማሪ መረጃ ይጠቀማል።

## የጣልቃ ገብ/የትምህርት ድጋፍ ውጤት “RtII” ጠቃሚ ቃላት

**በተማሪ መረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ማድረግ፤** ለተማሪ ስኬት የማቀድ ሂደት (የትምህርትና የስነ-ምግባር) የተማሪ መረጃን በማሰባሰብና መረጃውን በተመለከተ በመወያየት ይካሄዳል።

**የልዩ ትኩረት ግምገማ፤** የተማሪው/ዋን የትምህርት እና/ወይም የስነ ምግባር ሁኔታ በተመለከተ ለተወሰኑ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጀ አጭር የምርመራ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግምገማ ነው።

**ጣልቃ ገብቶ መርዳት፤** የተወሰነ ችሎታን ያለመና የተማሪ ሁለገብ እድገትን ለማፋጠን የተዘጋጀ ማስተማር ነው። (የተወሰኑ ጣልቃ ገብ ድጋፎች ቀደም ብለው የተዘጋጁና መደበኛ ጣልቃ ገብ ድጋፍ የሆኑ ሲሆን፣ ሌሎች የተወሰኑ ጣልቃ ገብ ድጋፎች ደግሞ በችግር መፍታት ሂደት ውስጥ ባለው ሁኔታ ላይ በመመሰረት የሚዘጋጁ ናቸው)።

**ክፍል1፤** ሁሉንም ተማሪዎች የሚደግፍ ሁሉ አቀፋዊና የተለያዩ ዘዴዎች።

**ክፍል 2፤** የተለያዩ ችግር ያላቸውን ተማሪዎች መርዳት ያለሙ የማሚያ ጣልቃ ገብ ድጋፎች።

**ክፍል 3፤** በክፍል 1ና 2 አስፈላጊውን ምላሽ (ውጤት) ላላሳዩ ተማሪዎች በየግል የሚደረግ መጠነ-ሰፊ የጣልቃ ገብ ድጋፍ።

**የቤተሰብና የትምህርት ቤት መተባበር ፤** ለተማሪዎች የመፍትሄ ሃሳቦችን በጋራ ለማፈላለግ የተማሪ ወላጆችና የትምህርት ቤት ሰራተኞች ሃሳቦችን በመለዋወጥ፣ በስምምነትና  በመተባበር አብረው ይሰራሉ፤   በጣልቃ ገብ ድጋፍ ውስጥ የተማሪ መረጃ የማሰባሰብና ውሳኔ የመስጠት ሂደት ውስጥ ወላጆች ይሳተፋሉ።

**ችግር ፈቺ ቡድን፤** ተባባሪ ቡድንን፣  ወላጆችን፣ የትምህርት ባለሙያዎችንና  ልዩ ባለሙያዎችን ጨምሮ፣  የተወሰኑ ድጋፍ የሚፈልጉ ተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል የጣልቃ ገብና የትምህርት ድጋፍ/ችግር ፈች ሂደትን የሚያከናውን ቡድን ነው።

**የለውጥ (የመሻሻል) ቁጥጥር፤** አስፈላጊ የትምህርተ-ነክ ውሳኔዎችን ለማድረግ የሚረዳ ሂደታዊ የተማሪ መሻሻል መረጃን መሰብሰብና መተንተን ነው።

**የጣልቃ ገብና የትምህርት ድጋፍ፤** ከፍተኛ የትምህርት ጥራት መስጠት ፣ በትምህርታቸው ወደ ኋላ ለቀሩ ተማሪዎች የሚሰጥ ተጨማሪ ጣልቃ ገብ ድጋፍና የለውጥ (የመሻሻል) ቁጥጥር፣ እንደዚሁም ጥናትና ምርምርን መሰረት ያደረጉ የማስተማር ሥራዎች ናቸው። ይህ የቁጥጥር መረጃ  ተማሪዎች ተገቢ (በቂ) ትምህርት እያገኙ መሆናቸውን ለመወሰንና አስፈላጊ የትምህርተ-ነክ ውሳኔዎችን ለማድረግ የሚረዳ ነው።